## በአጭር መንገድ ወደ ዕረፍቱ መግባት፣ 1ቆሮ 10፡1-11

እስራኤላዊያን ሁሉ በግብጻዊያን ባርነት ጭቆና ስለተሰቃዩ እግዚአብሔር ከባርነት ነጻ አውጥቷቸው የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ ሲጓዙ ሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ ነበሩ፡-

ሁሉም በእግዚአብሔር ኃያል ሥራ ከግብጻውያን ባርነት ነጻ ወጡ፤

ሁሉም በዓይናቸው እያዩ ቀይ ባህርን ከፍሎ አሻገራቸው፤ ሁሉም እንደገና ወደ ባርነት ሊመልሱዋቸው የተከታተሉዋቸው ፈርዖንና ሰራዊቱ በባህር ሲያሰምጣቸው ተመለከቱ፡፡

ሁሉም ወደ ሚወርሷት አገር በሚጓዙት ጉዞ ቀን በደመና ሌሊት በእሳት ዓምድ መራቸው፤

ሁሉም ከአንድ መንፈሳዊ ምግብ (መና) በሉ፤

ሁሉም ከአንድ መንፈሳዊ መጠጥ (ከዓለት የፈለቀ ውሃ) ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው መንፈሳዊ ዐለት ጠጥተዋልና፤ ያ ዐለት ክርስቶስ ነበረ።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በብዙዎቹ ደስ ስላልተሰኘ በበረሃ ወድቀው ቀሩ።

### እግዚአብሔር በእነርሱ ያዘነባቸው ምክንያቶች፡-

ጣዖት ያመለኩ በመሆናቸው፤ ዘጸ 32፡4-6፣

ከሞአብ ሴቶች ጋር ዝሙት በመፈጸማቸው፤ ዘሁ 25፡1-9፣ ጌታን ለምን ምግብና ውሃ በየዓይነቱ ሳይቋረጥ አናገኝም በማለት ስለተፈታተኑ ዘሁ 21፡5-6

መሪዎቻቸው በነበሩት በሙሴና በአሮን በእግዚአብሔርም ስለ አጉረመረሙ፤ ዘሁ 16፡41-49፣

በእግዚአብሔር ታላቅ ችሎታና መልካምነት ስለ አልተማመኑበት፤ ዘሁ 14

ሁሉም በተመሳሳይ ውጣውረድ ውስጥ ያለፉ ቢሆንም ከጥቂቶቹ በስተቀር የቀሩት ሁሉ አምላካቸውን አሳዘኑ፡፡

በ1ቆሮ 10፡1-11፣ የሰፈረው የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍል ይዘት ለመረዳት እግዚአብሔር እስራኤላዊያንን ከግብጽ ባርነት ነጻ በመውጣት ተስፋ ወደ ሰጣቸው ርስት ያደረጉት ጉዞ ሂደት ምን ይመስል እንደ ነበር ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡

- እግዚአብሔር አመጸኛ በነበሩት የግብጽ መሪዎችና ህዝብ ላይ የሙሴ እጅ ወደ ለምጻምነት በትሩም ወደ እባብ ከመለወጥ ጀምሮ እስከ ግብጻዊያን በኲር ሞት ድረስ 10 መቅሰፍቶችና 2 ዓይነት ታምራዊ ስራዎች በማሳየት የፈጸመማቸው ሥራዎች ግብጾችም ሆነ እስራኤላዊያን በሰማይና በምድር እንደ እርሱ ያለ አምላክ ማንም እንደሌለ በተጨባጭ መረጃ ያሳውቋቸው በተለይ እስራኤላዊያኑ እንዲታዘዙትና እንዲተማመኑበት የሚያደርግ ነበር፡፡ ዘጸ 9፡14-16፡፡
- 3 ታምራት የሰራው ግብጻዊያን ሂዱልን ብለው ከለቀቁዋቸው በኋላ ከጎሸም(ራምሴስ) ተነስተው በመጓዝ በፒሀሂሮት (ቀይ ባህር አጠገብ) ሰፍረው ሳሉ ፈርኦንና ሰራዊቱ ወደ ባርነት ሊመልሱዋቸው በተከታተሉዋቸው ጊዜ ከፊት ይመራቸው የነበረው የእግዚአብሔር መልዓክና የደመናው አምድ ወደ ኋላ ተመልሶ በግብጻዊያንና በነርሱ መካከል መግባት፤ እንዲሁም ህዝቡን ባህር ከፍሎ አሻግሮ በዚያው ባህር ውስጥ አሳዳጆቻቸውን በማስመጥ ያሳያቸው ከማንም ከምንም ሊያድናቸው የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

- እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውና ሊወርሷት ጉዞ የጀመሩት ምድር በእግዚአብሔር ታላቅ ታምራዊ ኃይልና ችሎታ እንዲሁም በታማኝነቱ ሙሉ በሙሉ ካልተማመኑና ከእርሱ ጋር ካልተስማሙ በስተቀር በእነርሱ ኃይል ሊያገኙዋት የሚችሉት አልነበረችም፤

  ዘሁ 13፡17-18 የአግዚአብሔር ፈቃድ ከባርነት ነጻ የወጣው ህዝብ በአጭር ቀናት (በ14 ቀናት አካባቢ) ወደ ተስፋይቱ ምድር መግባት ነበር፡፡ ግን እስራኤላዊያን እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ ቢያዩም የእርሱን ታምራዊ ችሎታና ታላቅ ኃይል በሚገባ ተረድተውና አምነው ከማንኛውም አስቸጋሪ ሁኔታና ኃያል ሰልፈኛ እንደሚያድናቸው በሙሉ ልብ የሚተማመኑበት ደረጃ ላይ ስለ አልደረሱ በጉዞ ላይ ሳሉ ጦርነት ቢነሳባቸው እንደ ሚፈሩ ስላወቀ በአቋራጭ መንገድ ወደ ከነዓን ምድር በመምራት ፈንታ ረዘም ባለው የበረሀው መንገድ የመራቸው ተጨማሪ አስተማሪ ሁኔታዎችና የመማሪያ ጊዜ ሊሰጣቸው ነበር፡፡

  ከዚያም በኋላ ከእርሱ በቀር ማንም ሊሰራቸው የማይችል ሰርቶ ያሳያቸው ተጨማሪ ድንቅ ስራዎች እነሆ፡
  - ያንን ሁሉ ከሁለት እስከ ሶስት ሚሊዮን የሚሆኑ እስራዔላዊያን ሕዝብ እርሻ በሌለበት በምድረ-በዳ ለረጅም ዓመታት መናና በጠየቁም ጊዜ ስጋ መመገብ መቻሉ፤
  - ሙሴ 40 ቀንና 40 ሌሊት ያለ ውሃና ምግብ ሁለት ጊዜ (ለ80 ሙሉ ቀናት) በህይወት ምንም ድካም ሳይታይበት አቆይቶ አሳያቸው፡፡ ዘጸ 24፡15-18 እና 34፡28-35
    (በሳይንስ ያለውሀ 3 ቀን ያለምግብ ቢበዛ 3 ሳምንታት ብቻ መቆየት እንደ ሚቻል ይነገራል)
  - መራራውን የአሊምና የማራ ውሀ አጣፈጠላቸው (በማራ)፡፡
  - ወንዝ በሌለበት ከዓለት ውሃ አፈለቀላቸው (በቃዴስና በራፊዲም 2 ጊዜ)፡፡
  - ሊዋጉዋቸው በተነሱት አማሌቃውያን ላይ ድል ሰጣቸው፡፡
  - የኮሬብ/ሲና ተራራ በጥቁር ደመናና ድቅድቅ ጨለማ ሸፍኖ ሰማይ በሚደርስ የእሳት ነበልባል ክብሩን ገልጦ ከእሳቱ ውስጥ በከባድ ድምጽ ተናገራቸው፡፡
  - ለ40 ዓመታት በየቀኑ ቀን በደመና ሌሊት በእሳት አምድ መራቸው፡፡
  - ለየትኛውም ሕዝብ የሌለው የሕይወታቸው መምሪያ ቅዱስ ህግ ሰጣቸው፡፡

በራባቸውና ውሃ በጠማቸው ቁጥር ያለ ምግብና ውሃ ለፈለገው ያህል ጊዜ ሊያኖረን ይችላል ብለው እርሱን ማመናቸውና መውደዳቸው፣ ማመስገናቸውም በማሳየት፣ ቢቀጥሉ በገጠማቸው ችግር ሁሉ የእርሱ ታምራዊ ስራ ሊያዩበት ይችሉ ነበር፡፡ እስራኤላዊያን ግን ለጥቂት ቀናት ሲርባቸውና ውሃ ሲጠማቸው ያጉረመርሙና መሪዎቻቸውን ሊጣሉ ይነሱ ነበር፡፡ ከዚያም አልፎ እግዚአብሔር በግብጻዊያን ላይ አንድ ወይም ሁለት ከባድ ታምራት በማድረግ ግብጻውያንን በማጥፋት እስራኤላዊያን ፈጥነው ነጻ ማውጣት ሲችል በሕይወት እንዲቆዩ ያደረገው ብዙ ታምራዊ ስራዎች በማድረግ ግብጻዊያን ብቻ ሳይሆን ዓለም ሁሉ የእግዚአብሔርን ታላቅ ማንነት እንዲያውቅ ነበር፡፡

በዘጸዓት መጽሐፍ ብቻ "እግዚአብሐርን እንድታውቁ/እንዲያውቁ /እንዲያውቅ ነው" የሚለው ቃል 18 ጊዜ ተጠቀሷል፡፡

ረጅም ጉዞ የሚጓዝ ሰው ቅድመ-ዝግጅት ያደርጋልና ለጉዞዋቸው ህዝቡና ሙሴ ምን ቅድመ-ዝግጅት ነበራቸው ያሰኛል፡፡ በእጃቸው ካላቸው ውስጥ ማንቀሳቀስ የሚችሉትን ሁሉ ይዘው ወጥተዋል ማለት ቢቻልም ግን ያ ለሁለት ወራት ያህል የሚያዘልቅ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር ግን ምንም ዝግጅት ማድረግ ሳያስፈልገው ሁሌ ለዘላለም የሚተርፍ በረከት ያለው ነው፡፡ ለእኛም ባስጀመረን የእምነት ጉዞ እርሱ ለምድርም ሆነ ለዘላለም የሚሆነውን በረከት ሁሉ በእጁ ነው፡፡

እስራኤላዊያን በጉዞ ላይ ሳሉ ያጉረመረሙት ምንም ችግር ሳያጋጥማቸው ሳይሆን ቀጥሎ የሰፈሩት ነገሮች ስለ ደረሱባቸው ነው፡-

1. ዘጸ 5:1-21፣ ፈርዖን እንዚድ የሚሉት ስራ ስለ ፈቱ ነው በማለት በግብጽ ሳሉ የሚሰሩት ሽክላ ቁጥር ሳይቀንስ ጭድም ራሳቸው ፈልገው አምጥተው እንዲሰሩ ስለ ታዘዙና ስራ አክብደውባቸው በቂ ሥራ አልሰራችሁም እያሉ ይገርፏቸው ስለ ነበር ነው፡፡
2. ዘጸ 14:11-12፣ እግዚአብሔር 10 መቅሰፍቶች በግብጽ ምድር በማድረጉ ከለቀቃቸው በኋላ እንደገና አሳዶ ቀይ ባህር አጠገብ እንደሰፈሩ ፈርኦንና ሰራዊቱ ወደ ቀድሞው ባርነት ሊመልሷቸው ተከታትለው ሲደርሱባቸው፤
3. ዘጸ 15:22-24፣ በሱር ምድረ-በዳ ውሃ ሳያገኙ ለ3 ቀናት ተጓዙ፡፡ ማራ በደረሱ ጊዜ ውሃው መራራ ስለ ነበረ ሊጠጡት አልቻሉም፡፡ የውሃ ጥም ስለ ከበዳቸው ሕዝቡ በሙሴ ላይ አጉረመረሙ፡፡ በበረሃ ውስጥ ያለ ውሀ ለ3 ቀናት መቆየት እንዴት ቻሉ የሚያሰኝ ነው፤
4. ዘጸ 16:1-2-4፣ በሲን ምድረ በዳ ሕዝቡ ስለ ተራቡ በሙሴ ላይ አጉረመረሙ፡፡ እግዚአብሔርም መና ሰጣቸው፡፡
5. ዘጸ 17:1-3-7፣ ሕዝቡ በራፊዲም የሚጠጡት ውሃ ባለመኖሩ ሲጠሙ በሙሴ ላይ አጉረመረሙ፡፡ ቁ 7 ላይ እግዚአብሔርንም ተፈታተኑት፡፡ በኮሬብ አጠገብ ባለው ዓለት ውሃ አፈለቀላቸው፡፡
6. ዘጸ 32:1-10፣ 21-28፣ 35፣ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ተራራ ወጥቶ ሳይመለስ ረጅም ጊዜ (40 ቀንና ሌሊት) በመቆየቱ፣ ሕዝቡ አሮንን ይመራን የነበረው ሙሴ ምን እንደሆነ አናውቅምና የሚመሩን ጣዖታት ስራልን ብለው የወርቅ ጌጣቸውን አውልቀው ሰጥተውት እርሱም በመሳሪያ በመቅረጽ የወርቅ ጥጃ አስደርጎ አሰራው፡፡ ሕዝቡም የወርቅ ጥጃውን አንተ አምላካችን ነህ አሉት፡፡ ጌታም 5 ጊዜ ያጉረመረሙትን ታግሶ በ6ኛው ማጉረምረም 3000 ሰው በሞት ቀጣ፡፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ የሚወዱት/የሚያከብሩት/የሚፈሩት ነገር ካለ እርሱ ጣኦት ነው፡፡
7. ዘሁ 14:1-9፣ በሰለሉት ምድር ያሉ ሰዎች ግዝፈት ብዛትና የብረት ሰረገሎች ስላላቸው ፈርተው ለውጊያ አንወጣም ባሉ ጊዜ ፡፡ ከኢያሱና ከካሌብ በስተቀር የቀረው ሕዝብ ወደ ተስፋይቱ ምድር አይገቡም አለ፡፡ ሊሰልሉ ከተላኩት 12 የነገድ ተወካዮች ኢያሱና ካሌብ ሲቀሩ ሌሎቹ ተቀስፈው ሞቱ፡፡
8. እነርሱ ግን ክፉ ተመኙ፡፡ ዘሁ 11:4-6፣ 10-15፣ በግብጽ ይበሉት የነበረው የተለያየ ነገር ተመኙ/ናፈቁ ፡፡ እነርሱ በጉዞ ላይ ሳሉ በየቀኑ ይመገቡት የነበረው በአብዛኛው መና ብቻ በመሆኑ ሰለቹ፡፡ ሙሴ ሕዝቡ በየድንካኑ ደጃፍ ሆኖ ሲያለቅስ በመስማቱ ተበሳጨ፡፡ ቁ 33-34፣ እግዚአብሔርም ሌላ ምግብ ለማግኘት የተመኙት ሰዎች በመቅሰፍት መታ፡፡ ለዓለማውያን ያላቸው ሀብትና ንብረት በቤቱ ሆነን ሳለ እኔ ለምን የአህዛብን ያህል ሀብትና ምቾት የለኝም ብሎ አለማማረር፤ በግብጽ ሳሉም የነበራቸው ኑሮ የሰጠው እግዚአብሔር ነበር፡፡ ለዓለማውያን መልካም ነገርን የሚሰጠው ራሱ አግዚአብሔር ነው፡፡ እኛም በዓለማዊነት ሳለን የነበረን ኑሮ እግዚአብሔር የሰጠንን ነበር፡፡ ወደ ዓለም ብንመለስ የሚደላን የሚመስለን ካለን ይብስብናል እንጂ አይደላንም፡፡ እግዚአብሔር ወደ ዓለም ስለተመለሱ አይባርክም (አይሸልምም)፡፡

9. ዘሁ12:1-14፣ ማርያምና አሮን እግዚአብሔር በእኛስ አልተናገረምን ሙሴ ምን የተለየ ነገር አደረገው በማለት በማጉረምረማቸው እግዚአብሔር ተቆጥቶ ማርያም በለምጽ ተመታች፡፡
10. ዘሁ 16:1-32 ቆሬን ዳታንና አቤሮን በመሪያቸው በሙሴ ላይ በአመጽ ተነሱ፡፡ በመጨርሻም እነርሱና ከአነርሱ ጋር የወገኑትን ሁሉ ከነቤተሰቦቻቸውና ንብረታቸው ጋር መሬት ተከፍታ ዋጠቻቸው፡፡
11. ዘሁ 16:41-49 ፣ በማግስቱም መላው የእስራኤል ሕዝብ በሙሴና በአሮን ላይ በማጉረምረም ተቃውመው ተነሱ፡፡ በሕዝቡም መካከል መቅሰፍት ቢጀምርም አሮን ስለማለደላቸው መቅሰፍቱ ቆመ፡፡ በዚህ ጊዜ የሞቱት ሰዎች ብዛት 14,700 ነው፡፡

12. ዘሁ 20፡1-5፣ 7-12፣ ህዝቡ የሚጠጡት ውሃ በማጣታቸው ስለተጠሙ በሙሴና አሮን ላይ ተነሱባቸው፡፡ እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን ዓለቱን ተናገሩት ብሏቸው ሳለ ሙሴ አለቱን በበትሩ ስለመታ፣ እግዚአብሔር እንደ ነገራቸው ቃል ስላልተናገሩ ሁለታችሁም ወደ ተስፋይቱ ምድር አትገቡም ተባሉ፤ ሙሴን ተራራ ላይ ወጥተህ በዓይንህ ታያታለህ፣ ነገር ግን አንተም አትገባባትም አለው፡፡ ዘዳ 32፡51፣ 3፡27፡፡
13. ዘሁ 21፡4-5-9፣ እስራኤላዊያን በጉዞ ላይ ሳሉ አሁንም በምግብና ውሃ እጥረት ትዕግስታቸው አልቆ በሙሴና በእግዚአብሔር ላይ አጉረመረሙ፡፡ እግዚአብሔርም መርዘኛ እባብ ላከባቸው፡፡ ምክንያቱም ይሄ ሁኔታ እንዲደርስባቸው ያደረገው በእርሱ ላይ ያላቸው መተማመን ምን ያህል እንደሆነ ለመመዘን ነበርና፡፡
14. ዘሁ 25፡1-9፣ ከሞአባዊያን ጋር ዝሙት ፈጸሙ፣ የፌጎርን በዓል በማምለክ ስለ ተባበሩ- 24000 ሰው አለቀ፡፡

እስራኤላዊያን ወደ ሚወርሷት ምድር ጉዞ ሲጀምሩም ሆነ በጉዞ ላይ ሳሉ በቀጣዩ ጉዟቸው ምን ዓይነት ችግር እንደ ሚገጥማቸው ቀደም ብሎ ያልተነገራቸውና እነርሱም ያልጠበቁት ነገር ቢደርስባቸውም እግዚአብሔር እነዚህ ነገሮች እንዲደርስባቸው ያደረገው በየጊዜው እያደረጋቸው ከነበሩ ኃያል ስራዎች፣ ወሰን አልባ ታላቅነቱና ኃያልነቱን በሚገባ አውቀው ወደ ሚተማመኑበትና አድርጉ የሚላቸውን ሁሉ ታዘው ወደ ማድረግ፤ በፈተናም ወደ መጽናት መድረሳቸውን ለመመዘን ነበር፡፡ (ዘዳ 8፥3፣ "ሰው ከእግዚአብሔር (ያህዌ) አፍ በሚወጣው በእያንዳንዱ ቃል እንጂ፣ በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር ሊያስተምርህ አስራበህ፤ አንተም ሆንህ አባቶችህ የማታውቁትን መና መገበህ፤") ሰውነት ምግብ የሚያስፈልገውን ያህል ነፍስ በእግዚአብሔር ቃል ይበረታል/ኀይሉ ይታደሳል፡፡ ይሄ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የሙሴን ሰውነትና ነፍስ ያለ ምግብና ውሃ 80 ቀናት በሕይወት ማቆየት ችሏል፡፡ እነርሱ ግን፡-

ጌታን ተፈታተኑ/ተሚገቱ፤ ብዙዎች በእባብ ተነድፈው ሞቱ፣ ለምንድነው የሚያስፈልገን ነገር ባስፈለገን ጊዜ የማናገኘው በማለት በእግዚአብሔርና በሙሴ ላይ ትዕግስታቸው አለቀ/ተቆጡ ዘሁ 21፡5፡6፣

አጉረመረሙ/አማረሩ/አላመሰገኑትም/አልታዘዙትም- ሙሴን ተጣሉት- ዘሁ 14፡29-34 ከ20 ዓመት በላይ እድሜ ያላቸው ሁሉ በምድረ በዳ እየተንከራተቱ አለቁ፡፡ የመጨረሻው ሰው ከሞተ በኋላ ነው ኢያሱና ካሌብ ከወጣቱ ትውልድ ጋር የተስፋይቱን ምድር ለመውረስ የዮርዳኖስን ወንዝ የተሻገሩት፡፡ ከግብጽ ወደ ከነዓን ምድር ጉዞ 14 ቀናት ያህል የሚፈጅ ሆኖ ሳለ 40 ዓመት የፈጀው በህዝቡ ያለማመን ኃጢአት ምክንያት ነበር፡፡

እግዚአብሔር ግን የሚፈታተኑት/የሚሚገቱት/የሚከራከሩት አይደለም፤

የሚያጉረመርሙበት/ቅሬታ የሚያሰሙበት/የሚያማርሩት አይደለም፤

የሚያኮርፉት፣ የሚቆጡት፣ የሚጠራጠሩት፣ የሚያስቀይም/የሚበድል አይደለም፤

ቅድመ ሁኔታ የሚያስቀምጡበትና አድርጉ ያለውን እንቢ ሊሉት የተገባው አይደለም፡፡ ምክንያቱም አርሱ ሰው/ፍጥረት አይደለም፡፡ የሚሳሳት፣ አንዳች ዓይነት እንከን ያለበት ሳይሆን ሁሌ ፍጹም ነው፡፡ እርሱ ሁሉ አዋቂ፣ በመንገዱና በማንነቱ ሁሉ ፍጹም ምንም መሻሻል የሚገባው መንገድ፣ ስርዓት፣ ባህርይ የሌለው ነውና፡፡ እኛ ሰዎች ነን አካሄዳችንን፣ ሀሳባችንን፣ ፈቃዳችንን፣ ባህርያችንን ከእርሱ ጋር ማስማማት ነው ያለብን፡፡ አንዳንድ ጊዜ ይሄን ወይም ያን ጉዳይ በዚህ ወር … ወዘተ ውስጥ ካላደረገልኝ/ካልሰጠኝ ከእግዚአብሔር እርቃለሁ የሚል ሰው የተሳሳተ ነው፡፡ ማለት ያለብን

የሚያስፈልገንን ነገር ጠቅሰን ይህን ነገር ይሰጠኛል/ሊሰጠን ይችላል፤ ግን ባይሰጠኝም እንደርሱ ያለ ለኔ ማንም ስለሌለ፤ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ አላመልክም ማለት ነው፡፡

በእነዚህ በየትኞቹ ድርጊቶች እግዚአብሔርን አሳዝነነው ይሆን፡፡ እስኪ ራሳችንን መርምረን ንስሀ እንግባ፡፡ ምን ውስጥ ገባሁ፤ ወደ ዓለማዊነት ልመለስ ብለን አስበን ይሆን? ክርስቲያን፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆናችን አሳንሰን አይተነው ይሆን?

**አንዳንዶች የእስራኤላውያን ከግብጽ ወጥቶ በምድረ-በዳ የመንከራተት ህይወትና ከነዓን መግባት ትምህርት ርእስ "መነሻና መድረሻውን እንጂ መሀሉ አይነገርም" ይሉታል፡፡ እኛም ቢሆን በወደፊት የክርስትና ጉዟችን መቼ ምን እንደ ሚገጥመን አናውቀውም፡፡ በሚገጥመን ማንኛውም ውጣ ውረድ እስከ ዛሬ ድረስ በኃይሉ ብርታት እየተዋጋልን እንዳደረሰን ወደ ፊትም በድል አድራጊነቱ ወዳየልን ግብ ያደርሰናል ብለን ማመን ነው እንጂ፡፡** የህዝቡ በምድረ-በዳ መንከራተትና መንገላታት የእግዚአብሔር እቅድ አልነበረም የህዝቡ አለመማንና ኃጢአት ውጤት ነው እንጂ፡፡ እግዚአብሔር ለህዝቡ የነበረው ዓላማ ከባርነት ነጻ በማውጣት፣ ባጭሩ መንገድ መምራትና የተስፋ ቃሉን/ርስቱን ማውረስ ሁሉ በታምራዊና ብርቱ ክንዱ ተጀምሮ ባጭር ጊዜ የሚያልቅ ነበር፡፡ ዘጸ 6፡6-8 (ዘሁ 32፡14-15)

የእኛስ የወደፊት ምድራዊም ሆነ ሰማያዊ ህይወታችን እጣ ፈንታ ምን እንደሆነ እናውቃለን ወይ፡፡ እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር ላወጣቸው ህዝቡ ያዘጋጀው የእረፍትና የልምላሜ፣ የስኬት ህይወት እንደነበረ ለኛም እንደዚሁ ነው፡፡ ሊበላሽ የሚችለው አካሄዳችን ከእግዚአብሔር ጋር ካላደረግን ብቻ ነው፡፡ ዮሐ 10፡10፣ "... እኔ ግን ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲትረፈረፍላቸው መጣሁ" ብሏልና፡፡

በዓለም ሳለን የሚገጥሙን ችግሮች እንዳሉ ተነግሮናልና የሚታወቅ ለኛ እንደ አቅማችን የተመደበ ከእምነታችን የተነሳ የሚገጥመን ስደት/ውጊያ፣ እግዚአብሔርም ብዙ ፍሬ እንድናፈራ የሚያደርግበት ሂደት ነው፡፡ ያም ሆኖ በእግዚአብሔር ታመንነን እርሱን በመታዘዝ ብንቀጥል ኃይሉን በህይወታችን የሚገለጥበት ዓለም ሊሰጠን የማይችል ሰላምና ደስታ የሚፈስበት ነው፡፡

እንዲህ ዓይነት ውጣውረድ ሲገጥመን በእግዚአብሔር ፊት የነርሱም ሆነ የኛ አቀራረብ መሆን የነበረበትና ያለበት፡-

1. **ሁል ጊዜ በፍርሀትና በአክብሮት፣ በትህትና በፊቱ መመላለስ፡፡** (ኢዮ 38፡2፣ "እውቀት በጎደለው ቃል እቅዴን እንዲህ የሚያጨላልም ማነው? አለ፤)
2. **ለታላቅ ማንነቱና ለቃሉ መገዛት/ታዛዥ መሆንን የሚመዝንበት ነው፡-** አድርጉ ያለውን/ፈቃዱን በደስታ በሙሉ ልብ በመነሳሳት ለማድረግ ራሳቸውን ማዘጋጀትና ሙሉ በሙሉ መገዛት- ጥቅሙ ለራሳችን ነውና ዘጸ16፡4፣ በጥቂት የታመነ ብዙ ይሾማል፡፡ እግዚአብሔር ከትንንሽ ነገር ጀምሮ የማንታዘዝ ከሆነ የበለጠ የአገልግሎት ጸጋ፤ የተሻለ የስራ ኃላፊነት፤ ከፍ ያለ ሀብት እንዴት ይሰጠናል፡፡ የሰጠንም ሆነ የሚሰጠን ነገር ሁሉ እኮ የእርሱ ነው፡፡ እኛ በሰጠን ነገር የእግዚአብሔርን ሀሳብ እንድናገለግልበት ባላደራዎች ነን እንጂ እንደፈለግን ልናደርገው አይደለም፡፡ መገዛት/ዝቅ ማለት ሳንማር ከሰጠን መታበይ ይመጣል፡፡ መታበይ ካለ ደግሞ ውደቀት የማይቀር ነው፡፡ ወድቀን ከምንቀር ባይሰጠን ይመርጣል፡፡

   እግዚአብሔርን የማክበር መገለጫዎች ከሆኑት ጥቂቶቹ ለመጥቀስ ያህል፡-
   በመካከላችን የመገኘቱ ምልክቶች ሲሰጥ/በቃሉ ልባችንን ሲነካ፣ መስገድ/ፊትለፊት መውደቅ/ማምለክ፣ መንበርከክ፤ በአክብሮት ንግግር ምላሽ መስጠት... ፡፡ ቅዱሳን ኃያላን መላእክት እንኳ እግዚአብሔርን ያመልካሉ (ነህ 9፡6፣ ኢሳ 6፡1-4፣ ራዕ 4፡6-11፣ 7፡11)

3. **ወደ እግዚአብሔር በእምነት መጸለይ/መጠየቅ፡-** የደረሰባቸውን ችግር እንዲያስወግድ/ የሚያስፈልጋቸውን ነገር እንዲሰጥ በትህትናና በአክብሮት መጸለይና እስኪፈጸም መጠበቅ፤

4. **ከኃጢአት መራቅ፡-** ኃጢአተኛ ግብጸውያን ያጠፉ፤ የከነአንን ምድር የኃጢአታቸው ጽዋ የሞላ ህዝቦች ሊያጠፉ ሰራዊት ይዞ ይጓዝ የነበረውን እግዚአብሔር በመፍራት ከኃጢአት መራቅ/አታድርጉ ያለውን አለማድረግ፡፡
5. **በእርሱ ላይ እምነት ያለን መሆኑን ለማረጋገጥ በየጊዜው እንደሚመዝነን አውቀን ለሚገጥመን ውጣ ውረድ ሁሉ የእምነት ምላሽ መስጠት፡-** በጉዞ ላይ ሳሉ የተለያየ ችግር ደርሶባቸዋል፡፡ ተራ በተራ የተለያየ ችግር እንዲደርስባቸው ይፈቅድ የነበረው በየደረጃው ካሳየው ታላቅ ማዳንና ከሰራው ታምራዊ ስራ ብዛት (ካስተማረው ትምህርት) የእርሱን ወደር አልባ ታላቅ ኃይል፤ ችሎታና መልካምነት ተምረው ታላቅ ማንነቱን አውቀው ማናኛውም ፈተናና ጠላት ሲገጥማቸው በእርሱ መታመናቸውን እንዲገልጡ/ የእምነት ምላሽ እንዲሰጡ ነበር፡፡ ዘሁ 14፡11፤ ችግር/ ውጊያ በሌለበት ቃሉን ማሰተማር ይቻላል እንጂ ታምራዊ ስራ መስራት አይቻልም፡፡ ችግሮች እግዚአብሔር ታአምራት አድራጊ አምላክ መሆኑን የማንነቱ ታላቅነት) ማሳያዎች ናቸውና፡፡
6. **ልዩ ልዩ ችግር ሲገጥም ችግሩ የእግዚአብሔር ታላቅ ማዳንና ታምራዊ ስራ አይበታለሁ ብለው መጠበቅ እንጂ አለመፍራት፡፡** 1ሳሙ 17፡37 "ከአንበሳ መዳፍና ከድብ መንጋጋ ያዳነኝ ከዚህ ፍልስጤማዊም ያድነኛል" ብሏል ንጉስ ዳዊት፡፡ በምድረ-በዳው ቢደላቸው ደግሞ ወደ ተስፋይቱ ምድር አንሄድም እዚሁ እንቆያለን ይሉ ነበር ይሆናል፡፡

7. **አለመሰልቸት፤-** መናው ሰለቸን አሉ፡፡ ለ40 ዓመታት ይህን መና የመገባቸው ለረጅም ዓታት ቢመገቡትም ሰውነታቸው ያልተጎዳው መናው ውስጥ ለሰውነታቸው የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ስላደረገበት ነው እንጂ የተለያየ የምግብ ዓይነት ማቅረብ ስላልቻለ አይደለም ብዬ አምናለሁ፡፡ እንዲያውም ጉዞ ጀምረው ጥቂት ከተጓዙ በኋላ በቂ ውሃና የሚመች ምግብ ሳያቋርጥ ቢሰጣቸው ኖሮ እዚሁ እንኑር ወደ ተስፋይቱ ምድር አንሄድም ሳይሉ ይቀሩ ነበር ይሆን? ራሳችንን ከሌሎች/በዓለም ካሉት ጋር ማወዳደር ትተን እግዚአብሔር በሰጠን የኑሮ ደረጃ፤ በሰጠን ኃላፊነት/አገልግሎት ማመስገንና መርካት ያሻል፡፡ (ፊሊጵ 4፡11፣ በማንኛውም ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን ተምሬያለሁ፡፡)
8. **በሰጠው የስልጠና ዓይነትና ጊዜ ልክ የእርሱን ታላቅ ማንነት በማወቅና በእምነት ማደግ በእርሱ በመተማመንና ለእርሱ በመገዛት፡-** ከሲና/ሆሬብ ተራራ ተነስተው ወደ ቃዴስ በርኔ (ፓራን ምድረ በዳ) ሲደርሱ በአግባቡ የሚማሩ ከሆነ የሰጠኋቸው ስልጠና የኔን ማንነት በማወቅና በሚወርሷት ምድር ነዋሪዎች ሁሉ ላይ ድል እንደምሰጣቸው በማመን ለማደግ በቂና ከበቂ በላይ ስለሆነ ርስታቸውን ለመውረስ ይገቡ ዘንድ ምድሪቱን እንዲሰልሉ ፈቀደ፡፡ የስለላው ውጤት ህዝቡ ሲሰማ ወየው ጠፋን/አለቀልን አሉ፡፡ ሁለት ሰዎች ብቻ እግዚአብሔር ከኛ ጋር ከሆነ መውረስ እንችላለንና እንውጣ አሉ፡፡

ከየነገዱ የተመረጡ ሰላዮች ተልከው ከስለላው መልስ ክፉ ወሬ ባመጡ ጊዜ የህዝቡ ምላሽ ማለቃችን ነው ብሎ መጮህ ነበር፡፡ በእምነታቸው ለውጥ/እድገት አላሳዩም፡፡

ዕብ 5፡12፣ "በዚህ ጊዜ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ ገና የእግዚአብሔር ቃል የመጀመሪያ ትምህርት የሚያስተምራችሁ ሰው ያስፈልጋችኋል፡፡ የሚስፈልጋችሁም ጠንካራ ምግብ ሳይሆን ወተት ነው፡፡" ከሚለው ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ተገኙ፡፡

እግዚአብሔር እስራኤላዊያንን ነጻ ያወጣው በኃጢአታቸው ምክንያት አመጸኛ ከነበሩ የግብጽ መሪዎችና ሕዝብ እጅ ነበር፡፡ የአብርሐም፣ የይስሃቅና የያዕቆብ ዘሮችን ከግብጽ ምድር ነጻ ያወጣውና ሊያስገባና ሊያወርሳቸው የነበረው ምድር ደግሞ ለብዙ ዘመናት እግዚአብሔርን ያሳዘኑና የኃጢአታቸው ጽዋ ሞልቶ፣ ከግብጽ ወንዝ ጀምሮ እስከ ታላቁ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ባለው ስፍራ እነ ከነዓናውያን፣ ፌርዛውያን፣ … ወዘተ አሥር ነገዶች ሰፍረውባት የነበረችው ምድርን ነበር፡፡

ይህንን እስራኤላዊያኑ ያውቁ ስለነበር እግዚአብሔር ኃጢአት በሰሩት ላይ ምን ያህል መቆጣቱን አይተው ደጋግመው ኃጢአት በመስራት/በመጠራጠር፣ እርሱን በማስቆጣት መቀጠል አልነበረባቸውም፡፡

ሁለት እግዚአብሔር የተደሰተባቸው ኢያሱና ካሌብ ሌሎቹ እስራኤላዊያን ያለፉበት ጥሩም ሆነ መልካም ነገር በእኩል ሁኔታ የደረሰባቸው ሆነው ሳለ ለሁለት ዓመታት እርሱ የሰራቸው ታላቅ ስራዎች ልብ ብለው በማየት ብቻ፤ በዓይናችን ካየናቸው አስፈሪ ሰዎችና ሁኔታዎች ሁሉ አምላካችን ሊያድነን ይችላል ብለው ስለተማመኑበት ነው፡፡

የጌታ ሐዋሪያት የሐዋሪያነት ኃላፊነት የተሸከሙትና ለእኛም መልካም አርአያነት ያለው የእምነት ኑሮ የኖሩት ጌታ ለሶስት ዓመታት ያህል በሰጣቸው ትምህርት ነው፡፡

እግዚአብሔር በሙሴና በአሮን አማካይነት በግብጻዊያን የባርነት ቀንበር ስር ለነበሩት እስራኤላዊያን የተስፋ ቃሉን በማውረስ የሚጎበኝበት ጊዜ ስለ ደረሰ፣ ነጻ አውጥቼ ተስፋ ወደ ሰጠኋችሁ ምድር አግብቼ አሳርፋችኋለሁ የሚል መልዕክት ሲያደርሳቸው የሰጡት የፈቃደኝነት የደስታና የእምነት መልስ ነበር፡፡

ዘጸ 4፥29-31፣ "ሙሴና አሮን ሄዱና የእስራኤልን ሕዝብ አለቆች በአንድነት ሰበሰቡ፤ 30 አሮንም
እግዚአብሔር (ያህዌ) ለሙሴ የነገረውን ቃል በሙሉ ነገራቸው። ታምራቱንም በሕዝቡ ፊት አደረገ። 31
ሕዝቡም አመኑ፤ እግዚአብሔር (ያህዌ) ስለ እነርሱ የሚገደው መሆኑንና መከራቸውን ማየቱን በሰሙ ጊዜ ተንበረከኩ፤ በስግደትም አመለኩት።"

ሆኖም ጥቂት እንደ ቆዩ ችግር ሲደርስባቸው ያ እምነታቸው አልቀጠለም፡፡ ዘጸ 5፥21፤

ሆኖም እግዚአብሔር ብዙ ታላላቅ ታምራዊ ሥራዎች በመስራትና ግብጻዊያንን በማሰገደድ ሕዝቡን ከእጃቸው ፈልቅቆ ካወጣ በኋላ 14 ቀናት ያህል በሚፈጅ አቋራጭ መንገድ መርቶ ወደ ርስታቸው ሊያገባቸው ቢፈልግም አነስተኛ ተግዳሮት ቢገጥማቸው ወደ ግብጽ እንደ ሚመለሱ ስላወቀ በእምነት እንዲጠነክሩ ለማስተማር ረዘም ባለ መንገድ መራቸው፡፡ ደጋግሞ ከምንም ከማንም ሊያድናቸው የሚችል አምላክ መሆኑን የሚያረጋግጡ ታምራዊ ሥራዎች በመስራት ቢያስተምርም መለወጥ ስላልቻሉ "ፈጽሞ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም" ብዬ በቁጣዬ ማልሁ"፣ ስላለ በምድረ ባዳ ቀሩ፡፡ መዝ 95፥6-11፤

ልጆቻቸው ግን እግዚአብሔርን በማመን ስለ ጸኑና አድርጉ ያላቸውን ስላደረጉ በአጭር ጊዜ ውስጥ በቀላል ውጊያ ምድሪቱን ወርሰው አረፉ፡፡ እግዚአብሔር ከሕዝቡ እምነት ሲያጣ ወዳዘጋጀው በረከት ለማድረስ በእምነት መጽናት እስከሚችሉ ድረስ በረጅም መንገድ ይመራል (ረጅም ጊዜ ይፈጃል፣ በረከቱን ከመውረስ መቅረትም ሊኖር ይችላል፡፡) ሕዝቡ በእምነት ጸንቶ የሚታዘዘው ሆኖ ሲያገኘው ግን በአጭር መንገድ (ጊዜ) ወደ አየለት በረከት ያገባል፡፡

እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን በግል የሰራው ድንቅ ስራ ምን ያህል እንደሆነ መቁጠር እንችላለን፡፡ ለሌሎች አማኞች ያደረገውና ያየነውም አለ፡፡ ከዚህም በላይ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል በሆነው

በመጽሀፍ ቅዱስ ሰፍሮ ያለው የእግዚአብሔር ታምራዊ ስራ ሁሉ በዓይናችን እንዳየነው የምንቆጥረው ነው፡፡

ስለዚህ ሁል ጊዜ በህጻንነት ከመመላለስ መውጣት ይኖርብናል፡፡ በየሳምንቱ በየወሩ በያመቱ የእርሱን ታላቅ ማንነት በማወቅ፤ በእርሱ ታላቅ ችሎታ በመተማመን፤ በመልካም ፍሬ፣ በጸጋ …ልናድግ ይገባል፡፡ እየደከምን እየተጠራጠርን ለብ እያልን የምንሄድ ሳይሆን እየተነቃቃን /እየበረታን/ትኩስ እየሆንን እንድንሄድ እግዚአብሔር ከኛ የጠብቃል፡፡ በምድረ በዳ ያለቁት እስራኤላዊያን እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ርስት መውረስ ነገር ጉዞ ጀምረው በነበሩት ሳይሆን በልጆቻቸው ተከናውኖ ያለቀ ጉዳይ ነው፡፡

እግዚአብሔር ለኛ ያዘጋጀው ምድራዊም ሆነ መንፈሳዊ በረከት ጉዳይ ግን ገና ስለ አልተዘጋ/ዕድሉ ስላለንና በረከቱ ከፊታችን የሚጠብቀን ስለሆነ ጊዜው ሳይረፍድ፣ ስላፈው የስንፍና ጉዟችን ንስሃ ገብተን ይህን ትምህርት ከተከታተልነበት ቀን ጀምሮ ምንም ዓይነት ተግዳሮት ቢገጥመን በአምላካችን ታላቅነትና እንደ ማይጥለን በመተማመን አድርጉ ያለንን ሁሉ ታዝዘን በማድረግ በአቋራጭ መንገድ (በአጭር ጊዜ) ያየልንን ጸጋ መውረስ ስለ ምንችል በእግዚአብሔር ፊት ቃል በመግባት የጽኑ እምነትና ታዛኝነት ጉዞ መጀመር አለብን፡፡ ኢ.ያ 1፡16-18፣

የሚዋጋን ጠላት ሁሉ ትንሽ ነው፡፡ እግዚአብሔር ግን ወሰን አልባ ታላቅ ነው፡፡

ኤልያስ ታሪኩ (ዶ/ር)፣ 2019 ዓ.ም.